አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ትምህርት ቢሮ

Biiroo Barnoota Bulchinsa
Magaalaa Finfinnee

City Government of Addis Ababa Education Bureau

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## መመሪያ ቁጥር 162/2016

### በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች በጨዋታ ላይ የተመሠረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

2016ዓ.ም
አዲስ አበባ

# በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ መመሪያ

ትምህርት የዕድገት ሁሉ ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ ለሁለንተናዊ ልማት መፋጠን ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ ትምህርት ተመራማሪና ችግር ፈቺ ዜጎችን ለማፍራት የሚያስችልና የህብረተሰቡን አመለካከት ወደ እድገት አቅጣጫ የሚመራ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶች ሳይንሳዊ ግኝቶች ጋር በማስተዋወቅ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ዕድገቶችን የሚያፋጥኑ ትውልድ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ

በሁሉም የመንግስት፣ የግል እና ባለቤትነታቸው በሌሎች በሆኑ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ትምህርት ቤቶች ወጥነት ያላቸው በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን አተገባበር እና አፈፃፀም እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአሁኑ ወቅት ያሉትን የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ ያሉ የማስተማሪያ አካባቢዎችን በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን ለመተግበር ወቅቱን ያገናዘበ ወጥነት ያለው መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህረት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 16(2) (ሠ) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 162/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ከተማ አስተዳደር"** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2. **"ትምህርት ቢሮ"** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፤
3. **"ትምህርት ቤት"** አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ እውቅና ባላቸው የመንግስት፣ የግል፣ የህዝብ፣ እና ባለቤትነታቸው በሌሎች በሆኑ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው፤
4. **"የላቀ ደረጃ"** ትምህርት ቤቶች የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው፣ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስታንዳርድን የሚያሟሉ መስፈርቶች የሚያሟሉ እና ለሌሎች ተሞክሮ ልምዳቸውን ማካፈል የሚችሉ ናቸው፤
5. **"የትምህርት ቤት አመራር"** በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምርት ቤት ተመድበው የሚሰሩ ር/ መምህር፣ አስተባባሪ እና የቅድመ አንደኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘርን ያካትታል፤
6. **"የትምህርት ማህበረሰብ"** ተማሪ፣ ወላጅ፣ ርዕሰ መምህራን፣ መምህራን፣ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ ሱፐርቫይዘር እና ትምህርት ቤቶችን በተለያየ መንገድ ሊደግፉ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤
7. **"ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት"** በተለየ ሁኔታ እንደ ትምህርት አቀባበላቸው እና ፍላጎታቸው ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ህጻናት ናቸው፤
8. **"በጫወታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ዘዴ"** ማለት ተማሪዎች በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች እና በመረጡት ጨዋታ ወደ መማር የሚመሩበት የትምህርት አቀራረብ ነው። በጨዋታ ላይ በተመሰረቱ ፕሮግራሞች ውስጥ ልጆች ፍላጎታቸውን ይቃኛሉ፤ ወሳኝ ማህበራዊ-ስሜታዊ፤ ራስን-መቆጣጠር፤ የልማት እና የትምህርት ክህሎቶችን መቅረፅ የሚዳበሩበት እና መምህራን ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ፣ የመጫወቻ እድል በመፍጠር እና ጨዋታቸውን እንዲያሰፉ በማበረታታት ፍላጎታቸውን እንዲከታተሉ ያግዛሉ።

9. "ልዩ ተሰጥኦ እና ተውህቦ" አብረው ከሚማሩ አቻዎቻቸው በተለየ ሁኔታ አለምን የሚገነዘቡ እና ተጨማሪ ስራ የሚፈልጉ ህጻናት ናቸው፡፡

10. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተደነገገው እንደ አስፈላጊነቱ በሴት ጾታ ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በትምህርት ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>አደረጃጀቶች</u>

4. <u>በክፍል ውስጥ አደረጃጀት</u>

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከተሉትን የክፍል ውስጥ አደረጃጀቶች ሊይዝ ይገባሉ፡፡

1. በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት መስፈርቱን ያሟላ የመማሪያ ክፍል፤
2. በተዘጋጁት ጭብጦች መሰረት የትምህርት ቁሳቁስ ጥግ ማደራጀት፤
3. በቂ ብርሃን እና አየር የሚያገኝ ክፍል ማዘጋጀት፤
4. ለጀማሪዎች የወለል ምንጣፎች አቅርቦት ያለው ክፍል፤
5. ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እድሜያቸው 5 እና 6 ለሆኑት ህጻናት ተስማሚ የሆኑ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ያሉት፣
6. በቂ የማሸለቢያ ክፍሎች ያሉት፣
7. ለህጻናት ተስማሚ የሆኑ፣ በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችሉ፣ የክፍሉን አደረጃጀት እንዳመቺነቱ ለመለወጥ የሚያግዙ የመጫወቻ ግብአቶች፣
8. በልጆቹ ቁመት ልክ የተዘጋጀ ሰሌዳ፣
9. ለመንቀሳቀስ ክፍት የሆነ ቦታ፣ ህጻናት ቁሳቁሶችን የሚያስቀምጡበት መደርደሪያ ወይም ቅርጫት፣ የመብራት አቅርቦት እና ሌሎች ተዛማጅ መሳሪያዎች፣
10. ወረቀቶች እና አስፈላጊ የጽህፈት መሳሪያዎች ማዘጋጀት፤
11. ለመንቀሳቀሻ ጥበት ያለበት ክፍል ከሆነ የቁሳቁሶች ቦታ በመለዋወጥ ወይ ለጊዜው ባንድ ቦታ በማከማቸት ክፍት ቦታ መፍጠር የሚያስችል እድሎች ያሉት ወዘተ ሊሆን ይገባል።

5. <u>በክፍሎቹ ውስጥ መደራጀት ያለባቸው ጥጎች (ኮርነር)</u>

1. በስርዓተ-ትምህርቱ የተቀመጡ ጭብጦች መሰረት በማድረግ ልዩ ልዩ ግንዛቤን በሚያስጨብጡ መጫወቻዎችና ቁሳቁሶች በራስ አቅም የቋንቋ፣ የአካባቢ ሳይንስ፣ የሂሳብ፣ የቤተሰብ፣ ወዘተ ጥጎች ማደራጀት፤
2. ለህጻናቱ እድሜ የሚመጥኑ የተረት፣ የስዕልና ሌሎች ጠቃሚ መጽሐፍት በራስ አቅም ተደራጅተው የሚገኙበት ማድረግ፤
3. የአሻንጉሊቶች፣ እንደ የቤት ቁሳቁስ ያሉ የእቃ እቃ መጫወቻዎችና አልባሳት፣ የማብሰያና የመመገቢያ፣ የውሀ መቅጃ ወይም መያዣዎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ሞዴሎች፣ መስታወትና ማበጠሪያዎች፣ ስልኮች፣ ቦርሳዎች፣ የምሳ እቃ፣ ሰሀኖች፣ እንዲሁም የትወና ቦታ የመሳሰሉትን በራስ አቅም ተደራጅተው የሚገኙበት ማድረግ፤
4. ለምርምር የሚያግዙ አሻንጉሊቶችንና ቁሳቁሶችን ጨምሮ አጉሊ መነጽሮች፣ ዛጎሎች፣ እፅዋት፣ የሰብል ዘሮች፣ ማግኔቶች፣ ብረታ-ብረቶች፣ ሚዛኖች እና ክብደቶች፣ የተለያዩ መለኪያዎችና ሜትሮች፣ ካሴቶች ወይም ሌሎች በአገር ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች በራስ አቅም እንዲኖሩ ማድረግ፤
5. የተለያየ ቀለም፣ ቅርፅ እና መጠን ያላቸው ቁሳቁሶች፣ የግንባታ ሞዴሎችን ለመስራት የተዘጋጁና የሚሰካኩ ከእንጨት ወይም ፕላስቲክ የተሰሩ ቅርጾች፣ መዶሻን የመሳሰሉ የግንባታ እቃዎች፣ ወዘተ እንዲኖሩ ማድረግ፤
6. ለተለያየ ቅርጾች መስሪያ የሚያገለግሉ ተለማጭ ቁሳቁሶች፣ ተገጣጣሚ ቅርጻቅርጾች ወይም ካርዶች፣ የሚደረደሩና የሚሰካኩ ቁሳቁሶች፣ ትናንሽ እንደ መኪና፣ እንስሳት ወዘተ. ያሉ አሻንጉሊቶችን፣ አባከስ እና ሌሎች ከአካባቢው የሚገኙ ጥራታቸውን የጠበቁ ቅጠላቅጠሎች፣ ድንጋዮች፣ ጠጠሮች፣ አሸዋዎች፣ እንጨቶች፣ አበቦች፣ ወዘተ በራስ አቅም የሚገኙበት አድርጎ ማደራጀት፤
7. የተለያዩ ቀለማት ያሉዋቸው ወረቀቶች፣ እርሳሶች፣ ማርከሮች፣ ባለ ቀለም ጠመኔዎች፣ የጨርቅ ቁርጥራጭ፣ ቀለማት፣ ብሩሾዎች፣ ፕላስተሮች፣ ቦርዶች፣ የቆዩ ጋዜጦች፣ እና የፈጠራ ምናብን ወይም ዝንባሌን የሚያበረታቱ ቁሳቁሶች በራስ አቅም ማደራጀት፤
8. የባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ደወሎች፣ ጎድጓዳ ሳህኖች የሚገኙበት፣ ቪዲዮዎች፣ ሙዚቃዎች የሚታዩበትና የሚሰሙበት፣ የዳንስ ወይም የባህላዊ

ውዝዋዜ ለማድረግ የሚያስችል መንቀሳቀሻን የሚያመች አካባቢ ያለው አድርጎ ማዘጋጀት፡፡

6. **<u>ከክፍል ውጭ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊደራጁ የሚገባቸው</u>**

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከተሉትን የክፍል ውጭ አደረጃጀቶች ሊይዝ ይገባሉ፡፡

1. የመፃህፍት እና የንብረት ክፍል ወይም ፔዳጎጂ ማእከል ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ህትመቶች፣ ለመምህራንና ተማሪዎች መገልገያ የሚውሉ የኦዲዮ ቪዥዋል መርጃ መሳሪያዎች ያሉበት ቤተ መፃህፍት እና የማስተማሪያ መርጃ መሳሪያዎች የሚዘጋጁበትና የሚከማቹበት ማዕከል መኖር አለበት።
2. አስተማማኝ የንጹህ መጠጥና መታጠቢያ ውሀ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ አለበት።
3. ለህጻናት ምቹ የሆነና ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ወንዶችን እና ሴቶችን እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ህጻናትን ታሳቢ ያደረገ አዘውትሮ ጽዳት የሚደረግለት ንፁህ የመጸዳጃ ቤቶች አገልግሎት፣የእጅ መታጠቢያዎች በህጻናት ቁመት ልክ የተዘጋጁ፣

7. **<u>የተስተካከለ የሰራተኞች አመለካከት</u>**

በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን ተግባራዊ ያደረገ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤

1. በአስተሳሰባቸው የተለወጡ እና በጨዋታ የማስተማር ጠቀሜታን የተረዱ፣ በዚህም ሳቢያ የየድርሻቸውን ለማበርከት የሚተጉ ርዕሰ መምህራን ወይም አስተባባሪዎች፣ ዋናና ረዳት መምህራን፣ ተንከባካቢዎች፣ ነርሶች፣ የጽዳትና የጥበቃ ሠራተኞች ያሉት፤
2. ሁሉም ትራንስፎርም ያደረጉ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቢሮ በተዘጋጀው ሞጁሎች እና ሌሎች ለማሰልጠን ተብለው በተዘጋጁ የስልጠና ላይ ተመርኩዘው የሰለጠኑ ሰራተኞች ያሉት፤
3. ትራንስፎርም ባደረጉ ትምህርት ቤቶች ማናቸውም አዲስ ተቀጣሪ ሰራተኞች የሙከራ ጊዜያቸው ላይ በልዩ ሁኔታ በተዘጋጀ የሥልጠና እና የሥልጠና ሂደት ውስጥ ያለፉ፤

መሆን አለበት።

8. **<u>የአካባቢ ማህበረሰብ እና ወላጆች</u>**

በትምህርት ቤቱ አካባቢ ያለው ማህበረሰብ እና ወላጆች በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴ በልጆች እድገት ላይ ያለውን አስተዋጽኦ በደንብ የተረዱ እና የትምህርት ቤቱን ጥረት የሚደግፉ፤ በቂ ግንዛቤ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

# ክፍል ሶስት

# የተለያዩ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት

## 9. የትምህርት ቢሮ

ትምህርት ቢሮ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻገር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ስልቶችን ይነድፋል፣ ስልጠናዎችን ለክፍለ ከተሞች ይሰጣል፣ ትምህርት ቤቶቹ በግብአት መጠናከራቸውን ያረጋግጣል፤
2. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ አፈጻጸም እንዲመጡ ያደርጋል፣ ልምድ ልውውጥ የሚደረግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጣራል፤ ከልምድ ልውውጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ያሰፋል፤
3. የቀዳማይ ልጅነት ልማት መርሃ ግብር መሰረት በማድረግ የሶስት ዓመት እቅድ ያቅዳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
4. በጨዋታ የማስተማር ስነ-ዘዴ በህጻናቱ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤
5. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ማሳያነት ወደ ሚበቁበት ደረጃ ማሸጋገር፤
6. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻሻሉ አውደ ጥናቶች ያዘጋጃል፤
7. ከተለያዩ አካላት ኃብትን ያፈላልጋል፣ የሀብት ክፍፍል ያደርጋል፤ በአግባቡ መያዙን ይከታተላል፣ ከክፍለ ከተማ የሚመጡ የኦዲት የውጤት ሪፖርቶችን በማየት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
8. ለሁለንተናዊ እድገት ግንባታ የስርዓተ ትምህርቱ አተገባበር የተቀናጀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
9. የተከታታይ ምዘናን ተግባራዊነት ይከታተላል፣ ያረጋግጣል እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
10. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻሻሉ የሚረዱ መረጃዎች መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፤
11. ይሄን መመሪያ ተግባራዊ በማያደርጉ ት/ቤቶች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ በየደረጃው ያለ አካል ተጠያቂ ያደርጋል፡፡
12. ቀጣይነት ያለው ግምገማ አፈፃፀምን ይከታተላል ፣ያረጋግጣል እና የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 10. የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት

የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻገር የሚያስችሉ በቢሮ የተነደፉ ስልቶችን ይተገብራል፣ ያስተገብራል፣ ስልጠና የወሰደባቸውን የተለያዩ ስልጠናዎችን ለትምህርት ቤቶች ይሰጣል፣ ትምህርት ቤቶቹን በግብአት መጠናከራቸውን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
2. ልዩ ተሰጥኦና ተውብዎ ያላቸውን ህጻናት እንዲለዩ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤
3. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ አፈጻጸም እንዲመጡ ያደርጋል፣ ልምድ ልውውጥ የሚደረግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጣራል፤ ከልምድ ልውውጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለቢሮ ይልካል፤
4. የቀዳማይ ልጅነት ልማት መርሃ ግብር መሰረት በማድረግ ከትምህርት ቢሮ በሚሰጠው እቅድ መሰረት የሶስት ዓመት እቅድ ያቅዳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
5. በጨዋታ የማስተማር ስነዘዴ በህጻናቱ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ በቅድመ አንደኛ ደረጃት ምህርት ቤት ተግባዊ ጥናት መደረጉን እገዛ ያደርጋል፤
6. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻሻሉ ለሚዘጋጁ አውደ ጥናቶች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ በተሰጠው ድምዳሜ መነሻነት አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
7. ኃብትን ያፈላልጋል፤ በአግባቡ መያዙን ይከታተላል፣ የኦዲት የውጤት ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ ከቢሮ ጋር በመሆን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
8. ለሁለንተናዊ እድገት ግንባታ የስርዓተ ትምህርቱ አተገባበር የተቀናጀ መሆኑን በድጋፍና ክትትል ያረጋግጣል፤
9. ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይገመግማል እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል
10. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻሻሉ የሚረዱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል ለቢሮ ያሰውቃል፤
11. በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚገኙ ወይም/ እና የሚፈጠሩ አዋኪ ጉዳዮችን መወገዳቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 11. የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት

የወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማሻገር የሚያስችሉ የተነደፉ ስልቶችን መተግበሩን ያረጋግጣል፣ ፍላጎት መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ ፋይዳ ይገመግማል፣ ትምህርት ቤቶቹን በግብአት እንዲሟሉ ልየታ ያደርጋል እና መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
2. ልዩ ተሰጥኦና ተውብዖ ያላቸውን ህጻናት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣
3. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ አፈጻጸም እንዲመጡ ያደርጋል፣ ልምድ ልውውጥ የሚደረግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጣራል፣ ከልምድ ልውውጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለክፍለ ከተማው ሪፖርት ያደርጋል
4. የቀዳማይ ልጅነት ልማት መርሃ ግብር ከክፍለ ከተማ የተሰጠውን መሰረት በማድረግ የሶስት ዓመት እቅድ ያቅዳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
5. በጨዋታ የማስተማር ስነ-ዘዴ በህጻናቱ ያመጣውን ተጨባጭ ለውጥ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተግባዊ ጥናት መደረጉን እገዛ ያደርጋል፤
6. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻሻሉ ለሚዘጋጁ አውደጥናቶች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ በተሰጠው ድምዳሜ መነሻነት አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
7. ኃብትን ያፈላልጋል፣ በአግባቡ መያዙን ይከታተላል፣ ኦዲት እንዲደረግ ያደርጋል፣ በኦዲ ት ሪፖርት መሰረት በማድረግ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤
8. ለሁለንተናዊ እድገት ግንባታ የስርዓተ ትምህርቱ አተገባር የተቀናጀ መሆኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
9. ተከታታይምዘናንተግባራዊነቱንይከታተላል፣ያረጋግጣል፣ይገመግማልእንዲሁምየማስተካከ ያእርምጃይወስዳል፤
10. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሻሻሉ የሚረዱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል እና ያሰውቃል፤
11. በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህር ቤት አካባቢ የሚገኙ ወይም/እና የሚፈጠሩ አዋኪ ጉዳዮችን እንዲወገዱ ያደርጋል፤
12. ለአካል ጉደተኛ ህጻናት ተስማሚና ምቹ የሆነ ምድረ ግቢ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

## 12. የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. በትምህርት ቤቱ የማስተማር ስነ ዘዴው ጨዋታ ተኮር እና የህጻናቱን የመማር ዘይቤዎች ከግምት ያስገባ እንዲሆን ያደርጋል፤
2. ለሁለንተናዊ እድገት ግንባታ የስርዓተ ትምህርቱ በተቀናጀ መልኩ ይተገብራል፤
3. ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ያደርጋል፣ መረጃ ይሰበስባል፣ ለህጻናቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ የምዘና ስርዓቱን ይገመግማል፤
4. የትምህርት ቤት ምቹ አካባቢ ለመፍጠር መሠረተ ልማትን ማሟላት፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፣
5. ኃብትን ያፈላልጋል፣ በአግባቡ ይይዛል፣ ኦዲት እንዲደረግ ሲጠየቅ ይተባበራል፤
6. ለሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስራዎች ወደ ተግባር ይለውጣል፤
7. ትምህርት ቤቱን የህብረተሰቡ ለማድረግ የወላጅ ተሳትፎን ያሳድጋል፤
8. በትምህርት አሰጣጡ ለሚያጋጥሙ ክፍተቶችን በተግባራዊ ጥናትና ምርምር በማድረግ ይፈታል፣
9. ትምህርቱን ተጨባጭ ለማድረግ ከአካባቢው ከሚገኘው ጸጋ ያዘጋጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣
10. ልዩ ተሰጥኦና ተውብዎ ያላቸውን ህጻናት ይለያል፣ መረጃ ይይዛል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣
11. ለአካል ጉደተኛ ህጻናት ተስማሚና ምቹ የሆነ ምድረ ግቢ እንዲኖር ያደርጋል፤

## 13. የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህር

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የማስተማር ስነ ዘዴ ውጨዋታ ተኮር እና የህጻናቱን የመማር ዘይቤዎች ከግምት ያስገባል፣
2. ለሁለንተናዊ እድገት ግንባታ የስርዓተ ትምህርቱ በተቀናጀ መልኩ እንዲሆን ያደርጋል፤
3. ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ያደርጋል፣ መረጃ ይሰበስባል፣ ለህጻናቱ ድጋፍ ይሰጣል፣ ምዘናው ያስገመግማል፤
4. የእለት የትምህርት እቅድ ያቅዳል፣ ይተገብራል፤
5. ልዩ ተሰጥኦና ተውብዎ ያላቸውን ህጻናት መረጃ ያደራጃል፤

6. የመማር ማስተማሩን ሂደት አካታች ያደርጋል፤
7. የመማሪያ ክፍሉን ጽዳትና ምቹነቱን ያረጋግጣል፤
8. የማዕዘን ጥጎችን ያደራጃል፣ ህጻናቱ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፤
9. ህጻናት እንደ ፍላጎታቸው መሰረት ሙሉ ድጋፍ እንዲያገኙ ከወላጅ ጋር አብሮ ይሰራል፡፡

## 14. <u>ቅድመ አንደኛ ደረጃ ሞግዚት</u>

የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሞግዚት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. የህፃናቱን ጽዳት ይቆጣጠራሉ፣ ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ፤
2. ህፃናቱን አገልግሎት መስጫ ክፍሎችና በግቢው ውስጥ ሲንቀሳቀሱ አደጋ እንዳይደርስባቸው ይከላከላሉ፤
3. ህጻናት መሰረታዊ ክህሎታቸው እንዲያዳብሩ እገዛ ይሰጣሉ፡፡

## 15. <u>የሱፐር ቫይዘር ተግባርና ኃላፊነት</u>

በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳው የሚመደብ ሱፐርቫዘር የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል

1. በሁሉም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የማስተማር ስነ-ዘዴው ጨዋታ ተኮር እና የህጻናቱን የመማር ዘይቤዎች ከግምት ያስገባ መሆኑን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ጉለቶች ካሉ ያርማል፣ እንዲታረም ያደርጋል፤
2. ለሁለንተናዊ እድገት ግንባታ የስርዓተ ትምህርቱ በተቀናጀ መልኩ በአግባቡ እየተተገበረ መሆኑን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
3. በሁሉም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ መደረጉን፣ ይከታተላል፣ የምዘና ስርዓቱን ይገመግማል ግብረ መልስ ይሰጣል፤
4. በሁሉም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ በክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ላይ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ አደረጃጀቶች እና አሰራሮች መተግበራቸውን ክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ መልስ ይሰጣል፤
5. ለሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስራዎች ወደ ተግባር መለወጣቸውን ክትትና ድጋፍ ይሰጣል፤
6. ትምህርት ቤቱ ከህብረተሰቡ ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑን ይከታተላል፣ ጉድለት ሲያገኝ ድጋፍ ያደርጋል፤
7. በትምህርት አሰጣጡ የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን ተግባራዊ ጥናትና ምርምር እንዲደረግባቸው ፍንጮችን ይሰጣል፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

16. <u>ህግን ተከትሎ ስለመስራት</u>

1. የህጻናቱ ምዘና በተቀመጠው መስፈርት የቅድመ አንደኛ ደረጃ የመማር ብቃት መመዘኛ መስፈርት እና የአጠቃላይ ዕድገት መመዘኛ መስፈርት እንዲሁም በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት የሚከናወን መሆን አለበት፤

2. ማንኛውም የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የማስተማር ስነ-ዘዴን  መተግበር ግዴታ አለበት፡፡

17. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖረው ሕግ</u>

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈነ ጉዳይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

18. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ቢሮው ይፋዊ ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፤ ነሃሴ2016 ዓ.ም**

**ዘላለምሙላቱ /ዶ/ር/**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርትምህርት ቢሮ ኃላፊ**